# “አዲሱን ወይን በአሮጌው አቁማዳ” የማይቻል ፖለቲካ

### ክፍል አንድ

**ዮናስ 12-24-14**

ከዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አኳያ የትኛውም “ሥርዓቱን ለመገንባት እተጋለሁ” የሚል ሃገር የዜጎችንና ህዝቦችን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በህገ መንግስትና በዝርዝር ህጎች አውጥቶ እና ሰጥቶ ማክበርና ማስከበር የመጀመሪያ ተግባሩና መሠረታዊ ጉዳዩ ቢሆንም፤ የሥርዓቱ ማእከል የሆነው ህዝብ በእርግጠኝነት ተጠቃሚ መሆን የሚችለው ህገመንግስታዊና ህጋዊ ማእቀፉን ተግባራዊ ማድረግ ከተቻለ ብቻ ነው፡፡

ከዚሁ አንጻር ሀገራትን የተመለከትን እንደሆነ በብዙ ሃገሮች ህገ መንግስታት ከተጻፉበት ወረቀት በላይ ዋጋ የሌላቸው ሰነዶች ሆነዋል፡፡ ይህ ደግሞ መንግስታቱ በኒዮ ሊበራል ሃይሉ እጅ በመውደቃቸውና የዜጎች መሰረታዊ የሆኑና ከዜጎች መንጭተው ለዜጎች መዋል የሚገባቸውን መብቶች ለድርድር ማቅረባቸውና አሳልፈው ለመስጠታቸው ዋናው መነሻ ነው፡፡ ከብዙ ሃገራት ልምድና የዚሁ ሰለባ ከሆኑ ሃገራት ተሞክሮ መገንዘብ እንደሚቻለው ለውጭ ሃይሎች ጣልቃ ገብነትና ተፅዕኖ ስር መውደቅ የሚፈጠረው የየሃገራቱ ገዢ ሥርዓቶችና ተቃዋሚዎች ህዝብን ማእከል ያደረገውን በተግባር ግን ስለሥልጣን ጥማታቸው በላቸው የተሳሳተ አሰላለፍ ነው፡፡ በሃራችንም ህገ መንግስቱ በሰነድነት ብቻ የተከበረ ሳይሆን በተግባር እንዲውል በማድረግም ረጅም ርቀት የተጓዝበት ተጨባጭ ሁኔታ ቢኖርም ስለ ስልጣን ጥማታቸው የሃይል አሰላለፋቸውን ከፈረንጆቹ ያደረጉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በየጊዜው በተለይም ምርጫ በደረሰ ቁጥር እያብጠለጠሉ አሳልፈው ሲሰጡና ደጅ በመጥናትም ስልጣን ሲቋምጡ ማየት የተለመደ ነው፡፡

የዚህ ጽሁፍ ዋነኛ መነሻም ይህንኑ እና በተግባር ከሚታየው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደታችን ያፈነገጡ በተለይም የፈንጆችን እጅ እያዩ ስለሚያድሩ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ማውጋት ነው፡፡ ወጋችንም ሁለት ደርዝ የሚኖሩት ሲሆን የመጀመሪያው ያለፉና ጸረ ዲሞክራሲያዊ የሆኑ ልምዳቸውን ዛሬም በመድገም ሂደት ላይ ስለመሆናቸው ማውጋት ነው። ሁለተኛው ደግሞ ትብብራቸውን እና ህጋዊ ማዕቀፉን መሰረት በመድረግ

የሚታዩ አፈጻጸሞችን በመቃኘት ህብረተሰቡ እራሱንም ሆነ በመገንባት ላይ የምትገኘውን ሃገር መጠበቅ የሚያስችለውን ስንቅ ማስታጠቅ ነው፡፡

ስለሆነም ትርክታችንን በሶስት ክፍሎች ቀንብበን የምንቀጥል ሲሆን ፤በመጀመሪያው ረድፍ ከዴሞክራሲዊ ሥርአት ግንባታ አኳያ ሃገራችን የምትገኝበትን ደረጃና ከህገ መንግስታዊ ሰነድነት ባሻገርም ያለውን ተግባራዊ እንቅስቃሴና የተቃውሞውን መንደር የወደቁ ሃገራት ተሞክሮ እና ሞክሮትም ያልተሳካለትን ፈረንጅ አምላኪነት ፖለቲካ የሚዳስስ ይሆናል፡፡ በሁለተኛው ገበታ ላይ ደግሞ ሰሞነኛውን እና ምርጫ 2007ን ታሳቢ ያደረጉ በሰላማዊ ሰልፍ ስም እየተቀነባበረ ያለውን ሴራና የሴራውን መነሾና የገዢ ሥርዓቱን አቋም ከህገ መንግስቱ ንድፈ ሃሳባዊ እና ተግባራዊ ክዋኔዎች አንጻር የሚዳስስ ነው፡፡በሶስተኛውና ጉዳያችንን በምናሳርግበት ትርክት ደግሞ የተዘጉ በሮችን እና ትክክለኛውን እንዲሁም የሚያወላዳ የሆነውን ዲሞክራሲያዊ አማራጮች መቃኘት ነው፡፡

በዚሁ አግባብ ወደ መጀመሪያው ትርክታችን እና ተቃዋሚ የሆነው ስብስብ ላሳለፍናቸው 23 ዓመታት በዲሞክራሲያዊ ሥርዓቱ ግንባታ ላይ የሚያነሷቸው መሰረት የለሽ ወሬዎችንና ተግባራዊ ሁኔታውን ወደምንመለከትበት አጀንዳ በአዲስ መስመር እንገባለን፡፡

ሃገራችን ተወደደም ተጠላ ባለፉት 23 ዓመታት የግልና የቡድን መብቶቸን በሰፊ ህዝባዊ ተሳትፎና እንቅስቃሴ በመታገዝ ተግባራዊ የተደረጉበት ሃገር ስለመሆኗ መካድ ከማንችልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል፡፡ ይህን የምንለው ዜጎች ሃሳብን በመግለጽ መብታቸው በመጠቀም ማንኛውንም ሃሳብ በህጋዊ መንገድ መግለጽ የቻሉበት ጥሬ ሃቅ ስላለ ነው፡፡ይልቁንም የግልና የቡድን መብቶች ለመከበራቸው ማጠየቂያ ከሚሆኑ ድንጋጌዎች ውስጥ በመጀመሪያው ደረጃ ላይ ከሚገኘው ሃሳብን የመግለጽ መብት አንጻር ጉዳዩን በጥልቀት ካየነው፤ ሃሳብን በነጻ የመግለጽ መብት ክዋኔ በህጋዊ አግባብ መሆኑ የመርህም ሆነ የሳይንሱ ጉዳይ ቢሆንም ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓቱ ግንባታ ሲባል ቸል መባሉ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ወጣም ወረደ በህገ ወጥ መንገድም ተቃዋሚዎቹ በየፊናቸው የሚያሰሙት ጩኸትና ወቀሳም በዚህ የሚገለጽና የግልና የቡድን መብት ስለመከበሩ የትም ሳንሄድ ከራሳቸው ከተቃዋሚዎቹ አንጻርም ማረጋገጥ የምንችልበት ሃቅ ነው፡፡መንግስትን ከመቃወም ጀምሮ በማንኛውም ጉዳይ ላይ ያላቸውን የተለየ ሃሳብ

በነጻነት  (ከነጻነትም ባለፈ ቅጣምባሩ የጠፋ ነጻነት) አራምደዋል፡፡ በጋዜጦች መጽሄቶች፣ ቲያትር ወዘተ ሰላማዊ ሰልፍና ህዝባዊ ስብስባ  ወዘተ የመሰላቸውን ሃሳብ በነጻነት አራምደዋል፤ እያራመዱም ነው፡፡ (የማጋፈር ፖለቲካ ሆኖ በክፍል ሁለት ትርክታችን በምናየው አግባብ ስለ አንድ ፓርቲ ሁለትና ሶስት አመራሮች የተለያዩ አስተያየቶች ቢሰጡንም ቢያንስ ልክ እንደ አምና ካቻምናው መድረክ የተባለውና ኢዴፓ የተሰኙ ፓርቲዎች ከሰሞኑ ‹‹የተሳካ›› ህዝባዊ መድረክ እና ሰላማዊ ሰልፍ ማድረጋቸውን ያጤኗል) ማሰብም ሆነ ያሰቡትን መግለጽ የሚያስጠይቅበት ዘመን አልፎ በማንኛውም ህጋዊና ሰላማዊ መንገድ የማሰብና ሃሳብን  የመግለጽ ነጻት ተግባራዊ ሆኗል ስንል የምንሞግተውም ለዚሁና ከዚሁ ተከትሎም የምናረጋግጥባቸው አብነቶች ስላሉን ነው፡፡ በሃገራችን የሚገኙ የግል ፕሬሶችም የሚጽፏቸውን መሰረተ ቢስ የተቃውሞ ሃሳቦች ስናስታውስና ለዚህ  ጸሁፍ በዋናነት መነሻ የሚሆነን ሰማያዊ ፓርቲ የሄደባቸውን ህገ ወጥ ርቀቶች ስናጤን በህገ ወጥ መንገድም ሃሳበን በነጻት መግለጽ የተቻለባት ሃገር መሆኗን ለመመስከር እንገዳደለን፡፡ያም ሆኖ ግን በህገወጥ መንገድ የሚደረግ ሃሳብን በነጻ የመግለጽ መብት ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደቱም ፋይዳ የሌለው በመሆኑ በዚያው መቆምና ከማስጠንቀቅ በዘለለ ማለቂያ የሌለው ትዕግስት እንደማያስፈልገን ግንዛቤ ሊያዝበት ይገባል፡፡ሌላ ከዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አኳያ ማጠየቂያ የሚሆነን የመደራጀት መብትንም በተመለከተ እንደ አሸን የፈሉ ፓርቲዎችን በመመልከት መከበሩን ማረጋገጥ የሚቻል ይሆናል፡፡

የቡድን መብትን ተግባራዊ ከማድረግ አኳያም ከሁሉ በፊት ዜጎች አፍ በፈቱበት ቋንቋቸው ያለገደብ የመጠቀም መብታቸው በተግባር ላይ የመዋሉንና የማንክደውን ሃቅ በመቀበል ሃገሪቱ የሄድችበትን ርቀት መገንዘብ ይቻላል፡፡ የባህልና የታሪክ እኩልነትም ቢሆን ተመሳሳይ ነው፡፡ ተቃዋሚዎቹ አሁንም የሚናፍቁት ትናት እና ከትናት ወዲያ የአንድ ብሄር ባህልና ታሪክ ብቸኛ መታወቂያ እንድትሆን ተፈርዶባት የነበረችው አገራችን የባህልና የታሪክ እኩልነትን በተግባር ላይ ማዋሏም ሃቅ ነውና ልንውጠው ግድ ይላል፡፡ እኚህን እና በተግባር የሚታዩ ሃቆችን መዋጥ ከተሳነንና መሰረታችንን እነዚሁ መብቶች ላይ ካላደረግን ጩኸታችን ሁሉ ባዶና የደንቆሮ እንደሚሆን ያለመጠራጠር ልናጤነው ይገባል፡፡

የአገራችን ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ሉዓላዊ የስልጣን ባለቤት መሆናቸውን ተከትሎም በአገራዊ ጉዳዮች በእኩልነት የመሳተፍ መብታቸው መከበሩን የማንከደውና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታውን ሂደት ረጅም ርቀት ወይም ከማይቀለበሰበት ደረጃ ላይ መድረስ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ያም ሆኖ ግን አሁንም ይህን ረዥም ርቀት የተጓዘ የግንባታ ሂደት ለመቀልበስ በሥርዓቱ ውስጥ የተሰገሰጉ ኪራይ ሰብሳቢ ሃይሎች ፈተና መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ዲሞክራሲያዊ መብትን ከለላ በማድረግ ያለፈውን ሥርዓት ለመመለስ የሚሹ ሃይሎች ስለመኖራቸውና በዴሞክራሲያዊ መብት ስም በተለይም ምርጫን ተከትሎ የሚፈጽሟቸው ጸረ- ዲሞክራሲያዊ ተግባራቶች መኖራቸውንና ዛሬም እየቀጠሉበት መሆናቸው ሊታወስና በጥልቀት ሊፈተሸ ይገባል፡፡ ስለሆነም በተለይ ምርጫን መሰረት በማድረግ ግን ደግሞ ከላይ የተመለከቱ እና ከዲሞክራሲያዊ መብት ጋር የተያያዙ የተመለሱ ጥያቄዎች እንደ አዲስ በማጋጋል በአብዛኛው ደግሞ ከሰብአዊ መብቶች ጋር አቆራኝተው በማራገብ ልክ እንደቀደመው የኒዮ ሊበራል ሃይሉን እጅ የመጠምዘዝ ድጋፍ እየሻቱ ስለመሆኑና ይህ ደግሞ በምንም ደረጃ ለእነርሱም ጭምር የማይጠቅም ስለመሆንና ሃገራቱም በውጭ ሃይሎች እጅ ጥምዘዛ ምንም ነገር ማድረግ የማትገደድበት ደረጃ ላይ መድረሷን ተጨባጭ መሳያዎች በማቅረብ ማሳየት ተገቢ ይሆናል፡፡ ይህ ስብስብ ይህን የሚያዋጣውን መንገድ መከተል የጀመረው ዛሬ ሳይሆን ትናንት ነበርና የዛሬዎቹን እና በሰላማዊ ሰልፍ ስም የዴሞክራሲዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደቱን አደጋ ላይ የሚጥሉ ተግባሮቻቸውን በተጫበጭ ማሳያዎች ከመመለከታችን በፊት ይህንኑ እና ተያይዞ የመጣውን ጸረ ዴሞካራሲያዊ ፍላጎት የምናይበትን ክፍል ሁለት ትርክት በሚገባ ማጤን እንዲቻለን እና በሶስተኛው ክፍል ትርክታችን በምናስቀምጠው የመፍትሄ አቅጣጫዎችና ተጨባጭ ሁኔታ ላይ መግባባት እንዲቻለን የተቃውሞውን ስብስብ ፈረንጅ አምላኪነት እና ከኒዮ ሊበራሉ ሃይል ጋር የነበረ ጋብቻ እና በፍቺ የተጠናቀቀ ጋብቻ ወደኋላ (ወደ ምርጫ 97 እና 2002) ተመልሰን መመልከት ግድ ይለናል፡፡

የቂጣ ወይም የስድብ ነገር ከተነሳ ተቃዋሚዎች በየኤምባሲው እየዞሩ ፈረንጆችን ሲማጸኑ የሚደርስባቸው ተግሳጽና ውርደት ሳይወሳ ቢታለፍ የምርጫ 97ን ታሪክ የተሟላ አያደርገውም፡፡ በማለት የተቃዋሚውን ፈረንጅ አምላኪነት የሚተርኩልን የወቅቱ

የኢህአዴግ ዋነኛ የምርጫ ተዋናይ  የአገራችን ተቃዋሚዎች እንደአብዛኛው በዲሞክራሲ ያልበለጸገ ህብረተሰብ ተቃዋሚ ከህዝብ ይልቅ በውጭ ቆንስላዎች ወይም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚተማመኑ ናቸው፡፡ የህልውናቸው ምንጭ ህዝብ ሳይሆን ኤምባሲዎች እንደሆኑ አድርገውም ይቆጥራሉ፡፡ እውነትም ከእያንዳንዱ አባላቸው መዋጮ በመሰብሰብና ጠንካራ ድርጅታዊ ስራ በመስራት የህዝቡን አመኔታ አግኝተው ወደ ስልጣን ከመምጣት ይልቅ የሚቀናቸው ኤምባሲዎችን መወጣጫ አድርገው ወደ ስልጣን መምጣት ነው፡፡ይሉናል።

ይህም ደግሞ ዛሬ ለደረሱበት ከኤምባሲዎች ጋር የሰጭና ተቀባይ ግንኙነት ውስጥ አስገብቷቸዋል፡፡ ኤምባሲዎች በመስጠት ተቃዋሚዎች በመቀበል በመካከላቸው ቁልጭ ያለ የተዋረደ ግንኙነት መገንባታቸውን ከሰሞኑ እንቅስቃሴያቸው መገንዘብ አይከብድም፡፡ በመሆኑም ኤምባሲዎች እንደሰጭ የፈለጉትን ያደርጉ እንደነበረው አሁንም ያደርጉላቸው ዘንድ ቢሹም የማይሳካና የተበላ ፖለቲካ ነው፡፡ በሞትና ህይወት መካከል የሚያቆይ ገንዘብ መስጠታቸውን ተማምነው ቢፈልጉ ይሰድቧቸዋል፡፡ወይም ያመናጭቋቸዋል፡፡ ፈረንጆች ያነሱትን መፈክር ወይም የነደፉትን ስልት እንዲያራምዱ በቀጭን ትዕዛዝ መመሪያ ይሰጧቸዋል፡፡ካልፈለጉ  ደግሞ ገንዘቡን ከልክለው ደጅ ያስጠኗቸዋል፡፡ ተቃዋሚዎች ደግሞ እንደተቀባይ ፈረንጆች የሰጧቸውን ተልዕኮ ሁሉ ይፈጽማሉ፡፡እንዳሉን የሁለት ምርጫዎች ባለወግ ዛሬም ምርጫ 2007ን ታሳቢ በማድረግ በተቃዋሚዎቹ ዘንድ እየተደረገ ያለው የ97ቱ ተመሳሳይ ነው።

ዛሬም በ97ቱ ተመሳሳይ በዚህ የሰጭና የተቀባይ ግንኙነት ፈረንጆች በገንዘባቸው የመሳደብ ችሎታን መግዛታቸውና በየኤምባሲው የሚዞሩ ተቃዋሚዎች ደግሞ ለእንጀራቸው ሲሉ የመሰደብና የመዋረድን ጣጣ ለመሸከም መፍቀዳቸው በተግባር እየታየ ነው፡፡  ከዚህ በመነሳት በየእለቱ በየኤምባሲው ሲዞሩ የሚደርስባቸውን ስድብና ውርድት ከኢትጵያዊው ኩራት ጋር አነጻጽሮ በቅን ልቦና ነገሩን የሚመረምር ሁሉ  የራሳቸውን ሰብአዊ ክብር ማስጠበቅ የተሳናቸው የተቃዋሚ አመራረሮች የዚችን አገርና የኩሩ ህዝቦቿን ክብር ለማስጠበቅ የሚቻላቸው እንዴት ነው? ብሎ ለመጠየቅ መገደዱ አይቀርም፡፡በእርግጥም በኢትዮጵያ የአርበኝነት የነጻነት ተጋድሎ ተጠልለውም ቢሆን የራሳቸውን ክብር ማስጠበቅ

የተሳናቸው የተቃዋሚ አመራሮች የኢትዮጵያን ክብር እንዴት እንደሚያስጠብቁ የሚያወቁት እነርሱና ፈጣሪያቸው ብቻ ናቸው፡፡

በምርጫ 97 ወቅት በተቃዋሚዎቹ ዘንድ ለተነሳው ትርምስ አንደኛው ምክንያት ፓርላማ በመግባትና ባለመግባት መካከል ከመወሰን ጋር የተያዘ መሆኑ አይዘነጋም ፡፡ ይህን ጉዳይ የሚያስታውሱን የኢህአዴጉ የምርጫ ተጠሪ ተቃዋሚዎቹ እና አመራሮቻቸው ፓርላማ ለመግባት እንዳልተወዳደሩ ሁሉ ፓርላማ ውስጥ መግባት አለብን የለብንም በሚል አጀንዳ በውስጣቸው መዋከብ ጀመሩ፡፡ ልዩነታቸውን መፍታት ሲያቅታቸው የመረጠን ህዝብ ፓርላማ መግባት እንዳለብንና እንደሌለብን ይወስንልን ዘንድ እናማክረው ብለው ተነሱ፡፡ በአዲስ አበባ በየክፍለ ከተማው ከጠሩት መድረክ በተጨማሪ የታዋቂ ሰዎች መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አባላትንና የመሳሰሉ መድረኮችን እየጠሩ ምክር ለግሱን አሉ፡፡‹‹ተቃዋሚዎችን የፖሊቲካ ትግል ምን እንደሆነ ለማስተማር ብዬ ነው አብሬያቸው የምሰራው›› እያለ መመጻደቅ ይቀናው የነበረው ብርሃኑም የዚህ ሃሳብ ዋነኛ አቃንቃኞች ከነበሩት መካከል አንዱ ነበር፡፡

በሁሉም ጉዳዮች ላይ ከህብረተሰቡ የላቅን ነን በሚሉት ተቃዋሚዎች ዘንድ አንዴ ከተመረጡ በኋላ ፓርላማ ለመግባትም ላለመግባትም መወሰን የእነርሱ ፈንታ መሆኑ የሚሳት አልነበረም፡፡ ነግር ግን በውስጣቸው የሚነሱ ልዩነቶችን አጣጥመው መፍታት ስለማይችሉና ከህዝቡ ጋር የመገናኘቱን አጋጣሚ ሌላ የአመጽ ቅስቀሳ ሊያደርጉበት ስለፈለጉ በተጨማሪ ደግሞ ግራም ስለተጋቡ የህዝብ መድረኮች እየጠሩ ፓርላማ እንዲገቡ የመረጣቸውን ህዝብ ተመልሰው ፓርላማ እንግባ ወይ ? እያሉ መጠየቃቸው በራሱ አስቀድሞም የከሰሩ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ጉዳይ ነው፡፡

በዚህ ምክንያት ቅንጀት ተበታትኖ ኢ.ዴፓና መኢአድ በየፊናቸው መሄዳቸው ሳያንስ በመኢአድና ኤዴፓ መካከል ያለው ልዩነት በየቀኑ እየሰፋ እንጂ እየጠበበ አልሄድ ብሎ የነበረ መሆኑን አንዘነጋም ፡፡ ይህን በተመለከተ የሁለት ምርጫዎች ባለወጋችን እንዲህ ያስታውሱናል ፡፡ከዚህ በመነሳት በመኢአድና በኢ.ዴፓ መካከል ያለውን ልዩነት ሳያረግብ ብርሃኑ የቅንጅትን አንድነት አስጠብቆ በከንቲባነት ለመመረጥ ተጣደፈ፡፡ለዶክተሩ የሁሉም ነገር ማጠንጠኛው የከንቲባነት መንበሩን መቆናጠጥ ስለነበር ለእርሱ ቅንጅትም

ሆነ ቀስተ ዳመና መኢአድም ሆነ ኤዴፓ የቼዝ ጠጠሮች ናቸው፡፡ በእያንዳንዱ እርምጃው እንደ አመችነቱ በተናጠል ወይም በቡድን የላቀ ችሎታ ባለው ኃይል ፊት ያጋፍጣቸዋል፡፡ ሲፈልግ ሰድቦ ለሰዳቢ ይሰጣቸዋል፡፡ ኢንጂነር ኃይሉን የሚፈልጋቸው ተሸክመው ወደ መንበረ ከንቲባነቱ እንዲያመጡት ስለነበር፡፡በአንድ በኩል እየተለማመነ በሌላ በኩል ግን ገንዘብና መረጃ እየሰጠ በሚያሰማራቸው ‹‹ቤዛ››ን በመሳሰሉ የግል ጋዜጦች ያሰድባቸዋል፡፡የቅንጅት ሚስጥሮች በተለይም ኢንጂነር ኃይሉን የሚመለከቱና በየጋዜጣው ይወጡ የነበሩ ውስጣዊ መረጃዎች ከዶክተር ብርሃኑ የሚፈልቁ እንደነበሩ በአንድ አጋጣሚ ያገኘሁትና ዶክተር ብርሃኑ እንዲህ ብለህ ጻፍ እያለ መረጃ ምክርና ገንዘብ ይሰጠው እንደነበር ያጫወተኝ በግል ጋዜጣ ውስጥ ይሰራ የነበረ ጋዜጠኛ ነው፡፡አሁንም የሰማያዊው ይልቃል 9ኙን ፓርቲዎች የፈለገው የብርሃኑን የከሸፈ ቼዝ ለመሞከር መሆኑን መጠራጠር የዋህነት ነው።መኢአድና አንድነት ሞክረው በእንጥልጥል ያቆዩትም የውህደት ጉዳይ የሃይሉ ሻውል በብርሃኑ የደረሰባቸውን ሸወዳ የቅንጅቱ ምትክ ነኝ በሚለው አንድነት ላይ ለመበቀል የታለመ መሆኑንም መጠራጠር ተገቢ ነው።አንድነትም 2007ን በፍኖተ ነፃነት ጋዜጣው መድረኩን እያሳጣ የሚገኘው ከ97ቱ በለመደው የከሰረ ፖለቲካ ነው ።የትናንቱ ሰማያዊም በኢትዮ ምህዳሩ ምህዳሩን እያናጋ የሚገኘው ለዚሁና ለተመሳሳይ አስቀድሞ የከሰረ ፖለቲካው ነው።

በተለያየ አጋጣሚ እንደሚታየው በበለጸጉ አገሮች የሚገኙ አክራሪ ኒዮ ሊበራሎች የአገሮችን ሉዓላዊነት ከሚፈታተኑባቸው መንገዶች አንዱ መንግስታት ህግና ስርዓት የማስከበር ችሎታ እንዳይኖራቸው በማድረግ ነው፡፡ የውጭ ኃይሎች ከእነርሱ ጋር ለሚቀራረቡና እጅ ነስተው ለማደር ዝግጁነታቸውን ለገለጹ ያልበለጸጉ አገሮች የተቃዋሚ ፖለቲከኞች እኛ እስካለን ድረስ ምንም አትሆኑም በሚል ምክር ህግ እንዲጥሱ ማበረታታቸው የተለመደ ነው፡፡ በራሳቸው የአስተሳሰብ ችግርና በዚህ ምክር ተገፋፍተው ስህተት የሚፈጽሙ ተቃዋሚዎች በቁጥጥር ስር ሲውሉም በመንግስት ላይ የእርዳታና የብድር መሳሪያቸውን ለጫና ማሳረፊያነት መጠቃማቸውም እንዲሁ የተለመደ ነው፡፡

እንደምናስታውሰውም  በእኛም ሃገር ከአካባቢና ማሚያ ምርጫ መጠናቀቅ በኋላ ከሶማሊያ ጣልቃ ገብነት ባልተናነሰ ገዝፈው የመጡት ጉዳዮች የጸረ-አሸባሪነት ህግና በውጭ ኃይሎች ፋይናንስ የሚንቀሳቀሱ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በኢትየጵያ ፖለቲካ ውስጥ ገብተው

ነገር እንዳያመሰቃቅሉ ለማድረግ የወጡ አዋጆች ናቸው፡፡የእነዚህ አዋጆች መውጣት ተከትሎ ተቃዋሚዎችና ለእነርሱ ያደላሉ ተብለው የሚታሙት የግል ፕሬሶች በኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳሩ ጠቧል የሚል መፈክር አንስተው መጠነ ሰፊ ዘመቻ ማካሄዳቸውን አሁንም እንደቀጠሉበት ነው፡፡

የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን የሚመለከተው ህግ ላይም ያለው ነገር ተመሳሳይ እና የሁል ጊዜም ሰልፍና ጋዜጣ ማዳመቂያ መሆኑ በተጨባጭ የሚታይ ሃቅ ነው፡፡ ትዝ ይለን እንደሆን በ97 ምርጫ በውጭ ኃይሎች የሚታገዙና ለእነርሱም የሚታዘዙ መንግስታዊ ያልሆኑ ደርጅቶች ሰፊ የፖለቲካ ዘመቻ ውስጥ ገብተው ነበር፡፡
ለዚሁ ውለታው ዛሬ የአፍሪካ ጉዳዮች የሂዩማን ራይትስ ዎችን ተጠሪነት የተጎናጸፈውን እና የያኔውን አክሽን ኤይድ ተጠሪ ዳንኤል በቀለን ያስታውሷል ።በገንዘባቸው በሰው ኃይላቸው በንብረታቸው ሁሉ ተጠቅመው በምርጫችን ውስጥ እጃቸውን ያላስገቡ የውጭ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ምናልባት ለመድሃኒት ያህል አይጠፉ ይሆናል፡፡ እጅግ አብዛኞቹ ግን በኢህአዴግ ላይ ያነጣጠረ የማጥላላት ዘመቻ ሲያደርጉ እንደነበር መካድ አይቻልም፡፡ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፈጽሞ የማይመለከታቸው ቢሆንም በምርጫ 97 የውጭ መያዶች ከሰሜን እስከ ደቡብ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ተወናጭፈዋል፡፡ የሁለት ምርጫዎች ባለወግ ይህን ጉዳይ በተመለከተ ሲያስታውሱም “በዚያ ወቅት በሶማሌ ክልል ለመስራት ፈቃድ የተሰጠው አንድ ውጭ መንግስታዊ ያልሆነ ደርጅት ሁመራ ላይ ህዝብን ለአመጽ ሲቀሰቅስ ተገኝቶ ከአገር እንዲባረር ተወስኖ ነበር፡፡“በማለት ነው።

ሁሉም ባይሆኑ የቀለም አብዮት በሚካሄድባቸው አገሮች ሁሉ ዋነኛዎቹ የትሮይ ፈረሶች ለዚህ ስራ ተብለው የተቃኙት ወይም እዚያው በእዚያው የሚፈጥሩት መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችናቸው፡፡ የገንዘብ አቅም ስላለቸው በገንዘብ እጦት የሚቋረጥ ስራ የላቸውም፡፡በሰብአዊ መብት ሽፋን የሚንቀሳቀሱ ስለሆኑም በየትኛውም አገር በማናኛውም ቀንና ስፍራ ተገኝተው ሃሳባቸውን ለመሸጥ አይቸገሩም፡፡ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በአብዛኛው የቀለም አብዮት ማስፈጸሚያ አድርጎ መመልከት በእኛ የተጀመረ ሳይሆን ራሳቸውን በቀለም አብዮት መሃንዲስነት እያስተዋወቁ የቀለም አብዮት የሚካሄድበት አገር ሲያፈላልጉ የሚውሉት ኃይሎችም በሙሉ የራስ መተማመን የሚገልጹት ስለሆነ እዚህ ላይ መከራከር ተገቢነት አይኖረውም፡፡

ከዚህ ለመገንዘብ እንደሚቻለው ከርቀት ሆነው አገሮችን በቀለም አብዮት ማተራመስ የሚፈልጉ ኃይሎች መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እንደ አንድ መተማመኛ መመልከት የጀመሩት የኢትዮጵያ መንግስት የበጎ አድራጎት ሰድርጅቶችን የሚመለከት ህግ ከማውጣቱ ቢያንስ ከአስር ዓመታት በፊት ነበርና ህጉን ማውጣቱ የዘገየ ካልተባለ በቀር የሚያንጫጫና የሁል ጊዜም አጀንዳ መሆን ባልተገባው ነበር፡፡

ስለሆነም አሁንም ለውጭ ሃይሎች እሪ የሚሉ ተቃዋሚዎች ቢኖሩም መንግስት ምርጫ የህዝብ ሉዓላዊነት ማረጋገጫ መሳሪያ መሆኑን ስለሚገነዘብ የውጭ ኃይሎች ህዝብን ተክተው ማንንም ወደ ስልጣን ማምጣት አይገባቸውም ብሎ ያምናልና በአቋሙ እንዲቀጥል ይጠበቃል ይገባልም፡፡ የዚህ ህግ መውጣት በራሱ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ነጻነት ከፍተኛ ትርጉም የነበረው ቢሆንም ፈረንጆቹና በእነርሱ ገንዘብ የሚተዳደሩት መንግስታዊ ያልሆኑ ደርጅቶች ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዲሁም የግሉ ፕሬስ በዚህ አዋጅ ላይ ያለማቋረጥ ቢዘምቱበት የዜሮ ድምር ፖለቲካ መጨረሻ ነውና አይገርመንም፡፡ የእራሳቸውን ስራ አልጨረሱምና ምርጫ በመጣ ቁጥር በቀለም አብዮት ወይም ደግሞ ስልጣን የመጋራት ጥያቄ ልክ እንደያኔው ዛሬም ከመድረኩ ሰዎች እየተደመጠ ነው።ይህ ደግሞ ስለዴሞክራሲያዊ ስርአት እያወሩ ከሚገኝ የትኛውም ፓርቲ የማይጠበቅና የከሰረ ፖለቲካ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።ይህን የከሰረ እና በ97ም ታስቦ የከሸፈ ፖለቲካ በተመለከተ የወቅቱ የኢህአዴግ የምርጫ አጋፋሪ በረከት ስምኦን እንዲህ ያስታውሱናል።

*መድረክ ከተደራጀ በኋላ ድርጅቱ መሪዎች ትልቁ ስራ የቅንጅትን መጽሃፍ ማንበብና ራሳቸውን በጆን ሻርፕ ንድፈ ሃሳብ ማስታተቅ ሆነ፡፡ ለዚህም ያመቻቸው ዘንድ ደርጅቱ አንዴ ስምንት ሌላ ጊዜ ደግሞ ስድስት ደርጅቶች ያሰባሰበው ትልቁ ድርጅት መሆኑን ያውጃሉ፡፡ ከዚህም አልፎ ትልቁ የተቃዋሚ ደርጅት የእኛ መሆኑ ኢህአዴግ ከመድረክ ጋር ብቻ መደራደር አለበት ይሉናል፡፡ ለመጀመሪያዎቹ አራት ወራት ብቻ የመድረክ ሊቀመንበር እንዲሆኑ የተመረጡት ዶክተር መረራም ጳጉሜ ሶስት ቀን ከአሜሪካ ድምጽ አማርኛ ክፍል ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ‹‹መንግስት ከምርጫ ጋር የተያየዘ ሁከት እንዳይፈጠር ከፈለገ እንደዚምባቡዌና እንደ ኬኒያ የስልጣን መጋራት ስምምነት ነው*

*የሚሻለው፡፡ በማለት የአመጽ ውጥናቸውንና ህገ መንግስቱ ከሚፈቅደው የምርጫ ሳጥን ውጭ ስልጣን ለመጋራት ያላቸውን ምኞት ይፋ እስከማድረግ ደረሱ፡፡*

*ዶ/ር በየነ ንግግራቸውን ሲጀምሩ ኢህአዴግ ምን ቢያስብ ነው መድረክን ከማይረቡ ደርጅቶች ጋር ጭምር ቁጭ ብሎ አንዲደራደር የሚጠይቀው? የሚል ይዘት ያለው ሃሳብ ማራመድ ጀመሩ፡፡ ‹‹መድረክ ከሁሉም ትልቁ ደርጅት በመሆኑ እዚህ ግባ ከማይባሉ ደርጅቶች ጋር ቁጭ ብሎ በመደራደር ጊዜውን ለማባከን እንደማይፈልግ ስለዚህም ድርጅቶቹ ሁሉ ወጥተው ኢህአዴግና መድረክ ብቻ ቁጭ ብለው እንዲደራደሩም ጠየቁ፡፡ ኢህአዴግ ለዚህ ጥያቄ መልስ ከመስጠቱ በፊት ግን ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሁሉ ‹‹እንዴት ሲደረግ ነው መድረክ ይህን የመሰለ የጥጋበኛ ንግግር የሚናገረው›› በማለት እልህና ቁጣ የተሞላበት ምላሽ መስጠት ጀመሩ፡፡ ኢህአዴግም በፓርቲዎች መካከል የማመረጥ አቅጣጫ እንደማይከተል የስነ ምግባር ደንቡ የጋራ በመሆኑ ሁሉም የመሳተፍ መብት እንዳለው በአጽንኦት ገለጸ፡፡*

ይህን ትርክት የምንደመድመው ከላይ በትዝታችን ላይ የኮምኮምናቸውን ተቃዋሚዎች ዛሬም አንዳች  ለውጥ ሳያደርጉ እና በባዶ እጅ መንጫጫታቸውን የተመለከተ የተሰራ የኪሳራ ሂሳብ  በተመለከተ ስማቸውን ያልገለጹ ግን ደግሞ ከሚንጫጩቱ ፓርቲዎች የአንደኛው አባል ፣ምናልባትም አመራር ሊሆኑ እንደሚችሉ ጽሁፋቸው የሚያስገነዝበን ሰው ‹‹ከምርጫ  ውጭ አማራጭ የለንም›› በሚል ርዕስ በኢትዮ ምህዳር ጋዜጣ ቅጽ 02 ቁጥር 90 ታህሳስ 8/2007 ዓ.ም ህትመት ላይ  ሰሞንኛ  የሆኑትን ጩኸቶች ታሳቢ አድርገው ካሰፈሩት ትርክት ላይ ከጉዳያችንጋር የተያያዙትን እና ቢያንስ በተቃዋሚዎቹ አካባቢ ያለውን እና እኛም ብለን የነበረውን እንዲሁም ገና ከምንተርከው ጋር የተያያዙትን ነጥቦች እንደወረዱ በማቅረብ ነው፡፡

‹‹… እኔ አሁንም በግልጽ በድፍረት መነጋገር ካልቻልን  የተቃዋሚ ፓርዎች ችግር አይፈታም፡፡ አንድ ነገር በግልጽ መነጋገር ካለብን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ‘ያለን ጠንካራ ነገር’ የአጀንዳና የሃሳብ ጥራት›› ብቻ ነው፡፡ በተረፈ  ኢህአዴግ እስካሁን በስልጣን ላይ የመቆየቱ ሚስጥር እንደ ድርጅት እርሱ ጠንካራ ሲሆን እኛ ደግሞ ደካሞች በመሆናችን ነው፡፡

‹‹…መስከረም በመጣ ቁጥር ስለ ኢህአዴግ መንገዳገድና እንዴት  እንደምንጥለው ብቻ ነው የጨነቀን እያልን የተለመደ ዘፈን በመዝፈን እስክስታ ውረዱልኝ ማለት አሁንም የሚታይ ሃቅ ነው፡፡ በውጭ ያሉ ተቃዋሚዎችም ለሽግግር መንግስት የሚሆን መዋቅር እስከ መቅረጽ ደርሰዋል፡፡ኅበዝ አንድን ፓርቲ ማሸነፍ የሚቻለው በመጀመሪያ ጠንካራና ደካማ ጎኑ ሲታወቅ ብቻ ነው፡፡….

ስለዚህ በግልጽ ያለንበትን ድክመት የሚፈትሽ የኢህአዴግንም ጥንካሬና ድክመት እየገመገመ  እስትራቴጂ መንደፍ የማይችል ፓርቲ ምርጫ በደረሰ ቁጥር ቢሮከር የሚያመጣው ለውጥ አይኖርም፡፡

…በአብዛኛው ተቃዋሚዎች ጋር ያለ ችግር የውጭ ዲፕሎማቶችን እንደ ችግር ፈቺ የማየት አባዜ ነው፡፡….. ተቃዋሚዎች የመጣንበትን መንገድና አሁንም አብዛኞቻችን እየሄድንበት ያለው መንገድ ግን  የሚያጠናክረን ነው ብዬ አለስብም፡፡››

"የአጀንዳና የሃሳብ ጥራት የተቃዋሚዎቹ ጠንካራ ጎን ነው" የሚሉን ጸሃፊ ከታች ከዘረዘሯቸውና ከላይ ከተመለከቱ ጉደኛ ችግሮች አኳያ እንዴት ሊሆን እንደሚችል ግራ የሚያጋባና እርሳቸውም ‹‹በድፍረት ብንነጋገር ይበጃል›› ብለውን ቢጀመሩም መድፈር እንደተሳናቸው ‹‹የአጀንዳ እና ሃሳብ ጥራት ›› አለው የሚሉት ተቃዋሚ እርሳቸው እንዳሉትም የውጭ ዲፕሎማቶችን ደጅ ባልጠናና ድርጅታዊ መዋቅሩ ባልተናጋ ነበር በሚል ማጠየቂያ እንሞግታቸዋለን፡፡ ያም ሆኖ ግን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደቱን በተመለከተ ከላይ በመርህም ሆነ በትዝታ ትውስታችን ተቃዋሚው የመጣበት መንገድና አሁንም እሄደ የሚገኝበት መንገድ ትክክል ያልሆነ መሆኑን መስክርዋልና ድፍረቱ ከዚህ በበለጠ እና በሌሎቹም ዘንዳ ቢቀጥል ለሃገራችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓተ ግንባታ ወሳኝ እንደሚሆንልን አያጠራጥርም፡፡ በመጨረሻም ፀሃፊው ‹‹ ከምርጫ ውጪ አማራጭ የለንም ›› በሚለው ትርክታቸው ካሰፈሩትና ሙሉ ለሙሉ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎችን ሊያስማማ የሚችለውን ነጥብ በመጥቀስ ይህን  ፋይል ዘግተን ሰሞንኛ የሆነውን እና በዴሞክራሲ ስም ጸረ ዲሞክራሲያዊ የሆነውን ጫጫታ አብደው ከሚያሳብዱትና በትውስታችንም ከተመለከቱት ሚዲያዎችና በሰብአዊ መበት ስም ከሚነግዱ አክራሪ

ሃይሎች አኳያ እያንሰላሰልን ግን ደግሞ የሰሞኑ ጫጫታ ጅማሮ ዛሬ ሳይሆን ካለፈው ትውስታችን ቀጥሎ ምርጫ 2007ን ታሳቢ ካደረገው ትምክህት የጀመረ መሆኑን ወደምናጠይቀበት ክፍል 2 ትርክታችን እንሻገራለን፡፡

‹‹በምርጫ ዙሪያ እኔ ያለኝ አቋ ምርጫ በመጣ ቁጥር ለውይይት የሚቀርብ አይደለም፡፡ ምርጫ ለእኔ የመርህ ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ ምርጫ በዚህች ሃገር ምትክ የሌለው የለውጥ መሳሪያ ነው፡፡ ፓርቲዎች ፣የሲቪክ ተቋማት፣ ኢህአዴግ፣ ህዝቡ እና በአጠቃላይም በምርጫ ውስጥ ተሳትፎ የሚያደርጉ አካላት ስራቸውንና ሃላፊነታቸውን በአግባቡ የሚወጡ ከሆነ ምርጫው እውነትም ምርጫ ይሆናል፡፡››ዴሞክራሲ ሂደት እንደመሆኑ መጠን ለውጡም የማይቀለበስና እያደገ የሚሄድ ይሆናል፡፡